# ነገና ዛሬ

ነገ የኛ አይደለም መተማመኛችን፧
ነገ ቁርጥ አይደለም ለመታረሚያችን፧
ነገ ቅርብ አይደል ከጉዞ ዕረፍታችን፡፡

ዛሬ የግላችን እኛ ነን ኃላፊው፧
ዛሬ ስጦታችን ከፈጣሪአችን፧
ዛሬ እድላችን በጎ ማድረጊያችን፧
ዛሬ ተጨባጭ ነው ለማንነታችን፡፡

ነገ ተስፋ ነው ዛሬን ላወቀበት፧
ነገ ዕዳ ነው ዛሬ ላለፈበት፧
ነገ ዕሩቅ ነው የማይደረስበት፧
ነገ ቁርጥ አይደለ የምንተማመንበት፡፡

ዛሬ ይቅር መባባል ለነገ ነፃነት፧
ዛሬ ተግቶ መስራት ለነገ እረፍት፧
ዛሬ መተዛዘን ማሰብ ለነገ አንድነት፧
ዛሬ መተባበር ለነገ እድገት፡፡

ዛሬን በመልካም ተግባር አንሙላው፧
ከትላንነት እንማር ካለ ያጠፋነው፧
ተግባራችን ስለሆነ የነገ መስካሪው፡፡

ትላንት ስላለፈን እንተው መፀፀት፧
ነገም ስለራቀ እናብቃ መመኘት፧
ዛሬ ሳያመልጠን እንጠቀምበት፡፡

ከ ኒኒ ለገሰ